# ክልል አቀፍ ምዘናዎች፥ ቤተሰቦች MCA እና MTAS ውጤቶችን ስለመጠቀም ማወቅ የሚያስፈልጋቸው ነገሮች

በእያንዳንዱ ጸደይ፣ የሚኒሶታ ተማሪዎች የፌደራል እና የስቴት መስፈርቶችን ለማሟላት የሚከተሉትን ምዘናዎች ይወስዳሉ፥

- MCA (የሚኒሶታ አጠቃላይ ምዘና)
- MTAS (የሚኒሶታ የአካዳሚክ ክህሎቶች ፈተና)

አብዛኛዎቹ ተማሪዎች MCA ይወስዳሉ፣ ነገር ግን ልዩ የትምህርት አገልግሎቶች የሚያገኙ እና የብቃት መስፈርቶቹን የሚያሟሉ ተማሪዎች ከዚያ ይልቅ MTAS መውሰድ ይችላሉ።

ሚኒሶታ ከፍተኛ ጥራት ያለው ትምህርት ለእያንዳንዱ ልጅ መስጠት ላይ ካለው ቁርጠኝነት ውስጥ ለእያንዳንዱ ተማሪ ጥብቅ ይዘት እና ትምህርት ተደራሽ ማድረግ ቅድሚያ የሚሰጠው ነው።

ግላዊ የተማሪ ሪፖርት (ISR) የእያንዳንዱን ተማሪ የጸደይ ጊዜ የMCA ወይም MTAS ውጤቶችን ይሰጣል።

ሁሉም ተማሪዎች ያንን የክፍል ደረጃ ሲያጠናቅቁ ማወቅ የሚጠበቅባቸውን መሠረት በማድረግ፤ ውጤቶቹ በሂሳብ፣ ንባብ፣ እና/ወይም ሳይንስ የተማሪው/ዋን የመማር ሁኔታ **አጭር ምልከታን** ይወክላል።




- የሚኒሶታ ከመዋዕለ ህጻናት -12 የአካዳሚክ መስፈርቶች በእያንዳንዱ የትምህርት ይዘት ሁሉም ተማሪዎች መማር የሚጠበቅባቸውን እውቀት እና ክህሎቶችን ይገልጻል። ሁሉም ተማሪዎች ከፍተኛ ጥራት ያለው ይዘት እና ትምህርት እንዲያገኙ የትምህርት ቤት ዲስትሪክቶች መስፈርቶችን እንዲያስቀምጡ ይገደዳሉ።
- የተማሪዎ የአፈጻጸም ደረጃ ያሟላል ወይም ከመስፈርቶቹ የላቀ ከሆነ፣ እነሱ በአካዳሚክ መስፈርቶቹ ላይ እንደተገለጸው በትምህርት ደረጃቸው የሚጠበቀውን እውቀት፣ ክህሎት እና ችሎታዎች እያሳዩ ነው ማለት ነው።




ውጤቶቹ የተማሪዎ የትምህርት እድገት አንዱ **መለኪያ** ነው። ውጤቶቹን ተማሪዎ በየትኛው ላይ በጥሩ ሁኔታ እየሰራ/ች እና በየትኛው ነገር ላይ ተጨማሪ እርዳታ እንደሚያስፈልጋቸው ለመለየት መጠቀም ይችላሉ። የተሟላ ስዕል ለማግኘት ተጨማሪ መለኪያዎችን መጠቀም ያስፈልጋል።

- የአፈጻጸም ደረጃ (አያሟላም፣ ያሟላል፣ በከፊል ያሟላል፣ ወይም የላቀ) በአንድ የትምህርት ዓይነት ላይ ከጊዜ በኋላ ያለውን እድገት ሊያመላክት ይችላል፣ ነገር ግን የ MCA/MTAS ውጤቶች በተለያዩ ዓመት ከተገኙት ጋር ሊወዳደሩ አይችሉም፣ ምክንያቱም መለኪያዎቹ ሊወዳደሩ አይችሉም።
- ትምህርት ቤቶች ውጤቶቹን አንድን የተማሪዎች ቡድን መደገፍ እና የማስተማሪያ ሰነዶችን ማሻሻል አስመልክቶ ውሳኔዎቹን ለመወሰን እንደ መምሪያ ሊጠቀሙ ይችላሉ፣ ነገር ግን አንድን ተማሪ ወደ ቀጣዩ የትምህርት ክፍል ለማዘዋወር እና ከፍ ወዳለ/የማሻሻያ ኮርስ ላይ ለመመደብ ብቸኛ ምክንያት መሆን የለበትም።
- የሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤት ተማሪዎች ውጤቶቹን በ ሚኒሶታ ስቴት ስርዓት ውስጥ ያሉ ኮሌጆች እና ዩኒቨርስቲዎች ባሉ ኮርሶች ለመመደብ ወይም በትምህርት ቤቶቹ ፕሮግራሞቹ ውስጥ ላሉ የ ድህረ ሁለተኛ ደረጃ ምዝገባ አማራጮች (PSEO) እና ኮሌጅ መጠቀም ፕሮግራሞች ይችላሉ።



ተማሪዎን መጠየቅ ያለብዎ ጥያቄዎች፥

- እንግሊዘኛ ስትማር/ሪ ያለህ/ሽ ጠንካራ ጎኖች ምንድን ናቸው እና ፈተና የሆነውስ ምንድን ነው?
- እርዳታ ለማግኘት ወይም ጥያቄ ለመጠየቅ ትምህርት ቤት ውስጥ ማዋራት የሚችሉት ማንን ነው?

የተማሪዎን መምህር መጠየቅ ያለብዎ ጥያቄዎች፥

- የተማሪየ እድገት ላይ ተጨማሪ ማሻሻያዎችን እንዴት ማግኘት እችላለሁ?
- በትምህርት ቤት ውስጥ ተማሪየን ሊያግዝ የሚችል ምን ድጋፍ አለ?

# ክልል አቀፍ ምዘናዎች ለሚኒሶታ የትምህርት እቅድ መረጃ ይሰጣል

## የመስፈርቶችን አፈጻጸም መከታተል

- እነዚህ መስፈርቶች ከተማሪ የመማር እና የትምህርት ሂደት የሚጠበቁት ምን እንደሆነ ይወስናሉ።
- ክልል አቀፍ ምዘናዎች [ተማሪው መስፈርቶቹን በመማር ረገድ ያለውን ቅጽበታዊ ምልከታን ያሳያል።
- የህዝብ ትምህርት ቤቶች እና ዲስትሪክቶች እነዚህን ውጤቶች የሚዛናዊ እና ሁሉን አቀፍ የምዝና ስርዓታቸው አንዱ አካል በማድረግ ይጠቀሙበታል።
- ከዲስትሪክቱ የምዘና ስርዓት (የመማሪያ ክፍል፣ ዲስትሪክት፣ እና የስቴት ምዘናዎች) የሚገኙ መረጃዎች በአንድነት መስፈርቱን የማስተማር እና የመማር ሂደቱን ያግዛሉ።

## ለፍትሃዊነት ቅድሚያ መስጠት

- ከሚዛናዊ እና ሁሉን አቀፍ የምዝና ስርዓት የሚገኝ መረጃ ዘራቸው ወይም የዚፕ ኮዳቸው ምንም ይሁን፣ እያንዳንዱ ተማሪ ከፍተኛ ጥራት ያለው ትምህርት ማግኘቱን ያረጋግጣል።
- የክልል አቀፍ ምዘና ውጤቶች ግልጽ ያልሆነ ኢፍትሃዊነት ያለበትን ቦታ ለመለየት እና ተስፋ ሰጭ የማስተማር ልማዶች ላይ ለማተኮር የተለያዩ የተማሪ ቡድኖችን፣ ትምህርት ቤቶችን እና ዲስትሪክቶችን ለመመልከት ሊረዳ ይችላል።

## የተረጋገጠ ውጤቶችን መስጠት

- የሚኒሶታ አስተማሪዎች እና የማህበረሰብ አባላት በርካታ ደረጃ ያለውን ፈተና በማዘጋጀት ላይ ተሳትፎ አላቸው እና በዚህ ሥራ ላይ ዋና አጋሮች ናቸው።
- ውጤቶች ሪፖርት ከመደረጋቸው በፊት ጥብቅ የሆኑ ማጣሪያዎች እና ማረጋገጫዎች
- እነዚህ ሁለቱም ክልል አቀፍ የምዘና ውጤቶች ተማሪዎቹ ፈተናውን በሚወስዱበት ጊዜ መስፈርቶቹን ስለመማራቸው የተረጋገጡ እና አስተማማኝ መለኪያዎች ናቸው።

ከማርች 2020 ጀምሮ፥ መምህራኖች እና ተማሪዎች በማስተማር እና በመማር፣ እንዲሁም በማህበራዊ እና ስሜታዊ ደህንነት ላይ ከፍተኛ እና ጉ[1]ል[2]ህ ለውጦችን አስተናግደዋል። በመሆኑም እነዚህ ለውጦች በተማሪ ውጤት ላይ ሊንጸባረቁ የሚችሉ እና ነገር ግን በትክክል መለየት አስቸጋሪ ስለሆነ፣ የምዘና ውጤቶች ሲተረጎሙ ይህን ግምት ውስጥ ማስገባት አስፈላጊ ነው።

ጥያቄዎች?

ትምህርት ቤትዎ የተማሪን መማር በመደገፍ እንዴት እያከናወነ እንደሆነ የበለጠ መረጃ ለማግኘት፣ የፈተና ውጤት ደረጃዎች፣ የፈተና ውጤቶች እና ተሳትፎ ገጽን በ ሚኒሶታ ሪፖርት ካርድ ላይ የሚገኘውን ይጎብኙ።

ስለ ተማሪዎ የ MCA ወይም MTAS ውጤቶች ጥያቄዎች ካሉት፣ ትምህርት ቤትዎን ያግኙ። ስለ ሚኒሶታ የአካዳሚክ መስፈርቶች ወይም ምዘናዎች ጥያቄዎች ካሉት፣ ያግኙ mde.testing@state.mn.us።

DEPARTMENT OF EDUCATION